የመንፈሳዊ መረሃ ግብር አመራር ዘዴ

መግቢያ፡- መረሀ ግብር መምራት ማለት የተዘጋጀውን መንፈሳዊ ጉባኤ በታቀደለት አላማ ግቡን እንዲመታ በስርኣት መርቶ እንዲጠናቀቅ ማስቻል ነው። አነድ መረሃ ግብር መሪ ጉባኤው እንዴት እንደሚከናወን እንዴት እንደሚፈጸም እና ለኢይም አገልግሎት የሚያስፈልጉ እቅዎችን ሁሉ አውቆ መምራት ተገቢ ነው።ሠ መረሃ ግብር የንግግር ችሎታ ስላለን ብቻ የምንመራው አይደለም ምክንያቱም መንፈሳዊ ጉባኤ የራሱ የሆነ ጠባኤዎችና አካሄድ አለው።

ምዕራፍ አንድ

መንፈሳዊ መረሐ ግብር

ቤተክርስቲያን የተለያየ መረሐ ግብሮችን ዘርግታ ስለአምላካችን እንድናውቅ ምግባር ትሩፋትን እንድንሰራ የስሙ ቀዳሾች የክብሩ ወራሾች እንድንሆን ሁለትና ሶስት ሆነን በስሙ እንድንሰበሰብ ታደርጋለች ማቴ 18፤20 እነዚህ ጉባኤዎችም የቅዳሴ የኪዳን የሰዓታት የማህሌት የአብነት ትምህርት ቤት የስብከተ ወንጌል የሰ/ቤት እንዲሁም ከግቢዋ ውጭ የምትፈጽማቸው የጥምቀትና የመስቀል ደመራ ጉባኤዎች አፈጻጸማቸው የተለያ ይሁን እንጅ የቤተክርስቲያናችን ስርዓትና ትውፊት የጠበቁ እስከሆኑ ድረስ መንፈሳዊ መረሐ ግብሮች ይባላሉ። ቤተክርስቲያንይህንን መረሐ ግብር ስታከናውን ሁሉንም ሰው በአንድ አይን በመመልከት በፍቅርና በእንክብካቤ በመያዝ እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ እነደታዘዘ ለሰማያዊ ክብር ማብቃት ዋና ተግባሯ ነው።

1.1 መንፈሳዊ ማኅበር በዘመነ ብሉይ

አስራኤላውያን በአንድነት በመሆን ሲፈጽሟቸው የነበሩ ተግባሮች እንደነበሯቸው ይታወቃል። በእግዚአብሔር ማኅበር ተብሎ ሲጠራ የነበረው በሀዲስ ኪዳን ተብሎ ተጠርቷል። ቤተክርስቲያን ማለት አቅሌስያ ከሚለው የግሪክ ቅል የተወሰደ ነው።

1.2 መንፈሳዊ ማኅበር በዘመነ ሐዲስ

በዘመነ ሀዲስ ግን ከዘመነ ብሉይ በተለየ ደምቆና ያታያል።

1.3 መንፈሳዊና ዓለማዊ ማህበር ያላቸው ልዩነት

መንፈሳዊ መረሃ ግብር

- ጉባኤው በጸሎት ተጅምሮ በጸሎት ያልቃል
- በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በህገ ቤተክርስቲን ይከናወናል
- ታዳሚዎች ህገ ቤትክረስቲያንን የጠበቀ አለባበስ ይለብሳሉ
- ጉባኤውን የሚመሩ ሰዎች ፈሪሃ እግዚአብሔር አላቸው
- አላማው በምድር ላይ በጥሩ ህይወት እንዲኖሩና ከሞት ያለውን ዘላለማዊ ህይወት አግልቶ በማሳየት የሰሙ ቀዳሾች የመንግስቱ ወራሾች ማድረግ 2 ኛ 5፤1 ገላ 4፤7
- በጉባኤው የሚነገረው ስለእግዚአብሔር ቸርነት፤ አምላክነት፤ የማዳን ስራ፤ ስለክብረ ቅዱሳን...ስለመንፈሳዊ ህይወት ሰለጾምም፤---ይናገራል።

አለማዊ መረሐ ግብር

- ያለጸሎት ተጀምሮ ይፈጸማል
- ሰዎች ባወጡት ህግ የከናወናል
- ያለፈቃደ እግዚአብሔር ይጀመራል
- ለፕሮቶኮል ካልሆነ የወደዱትን ልብስ ይለብሳሉ

ምዕራፍ ሁለት

መረሃ ግብር መሪ

የቤተክርስቲያን ስርአት እምነት ትውፊት ጠብቀው የሚከናወኑ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ጉባኤዎችን የሚመራ ሰው መረሃ ግብር መሪ እንለዋለን። ያለመረሃ መሪ መረሃ ግብር አይከናወን ም።መረሃ ግብር መሪ በእለቱ ለተዘጋጀው መረሃ ግብር አላማ መሳካት ከፍተኛ ስራ በመስራት ትልቁን ድርሻ ይይዛል። ስለዚህ አንድ መረሐ ግብር መሪ ፈዞ ደንግጦ ቸለልተኛ ሆኖ ተደናግጦ... መቅረብ የለበትም። መረሃ ግብር መምራት ቀላል ስራ አድርጎ ማየትስህተትም ነው አከባሪውንም ማቅለል ነውና መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም መረሃ ግብሩ በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቁና ታዳሚውን ደስ ለማሰኝትና እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ለማድረግ መረሃ ግብር መሪው ትልቅ ሚና አለውና። መረሃ ግብር መሪው በትክክል ካልመራው የተዘጋጀው መረሃ ግብር ግቡን ሊመታ አይችልም።

መረሃ ግብር መሪ የሚከተሉትን መምሰል አለበት፡-

1. እንደ ንብ ታታሪ

ንብ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል የሚታፍት ለሰውነት የሚስማማ ለመዳኒት የሚያገለግል አድረጋ ታዘጋጃለች ። ንብ በትጋት እንደምትሰራ መረሃ ግብር መሪውም ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር ለማስተማር ቃለ እግዚአብሔርን ጠይቆ መጻህፍትን አንብቦ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ተዘጋጅቶ አውደምህረት መውጣት አለበት። ንቦች ሲሰሩ በህብረት እነደሆነ መረሃ ግብር መሪም ከወንድሞቹ ጋር ተባብሮና ተስማምቶ ሊሆን ይገባል።

2. እንደመኪና ሹፌር ጠንቃቃ

   አንድ የመኪና ሹፌር መኪናን ለማሽከርከር ማሰልጠኛ ተቋም ሰልጥኖ ህገዘብንና እቃን ሚፈለግበት ቦታ ያደርሳል። መረሃ ግብር መሪም ለመምራት ከመጀመሩ በፊት ስልጠና/ትምህርት/ያስፈልገዋል። ስልጠናውን አጠናቆ ወደ አገልግሎት ከገባ በኋልም እንደ መኪና ሹፌር ጠንቃቃ ሊሆን ይገባዋል።

3. እንደ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ሀላፊነት የሚሰማው

   ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ጌታችንን ለህዝቡ ለማስተዋወቅ አላፈረም፤ከፍ ሲያደርጉት ውዳሴ ከንቱን ከመቀበል ይልቅ ትህትናን ገንዘብ አደረገ ተልዕኮው ክርስቶስን ማስተዋወቅ ነውና ተልዕከውን ፈጸመ። መረሃ ግብር መሪም የራሱን ክብር ሳይሻ ተልዕኮውን መፈጸም አለበት።

4. ግብዣ እንዳዘጋጀ ሰው

5. እንደ አስጢፋኖስ ሰማኣት/ምስክር/

ምዕራፍ ሶስት

የመረሐ ግብር መሪ ህይወት

መረሃ ግብር መምራት ትልቅ አገልግሎት ነው። እግዚአብሔር በሚከብርበት ስሙ በሚጠራበት በቅዱሱ ስፍራ በተቀደሰው ስፍራ/ቤተመቅደስ/ ለማገልገልም ሆነ ለመገልገል መቀደስ (ራስን መለየት/ማዘጋጀት) ያስፈልጋል። መረሃ ግብር መምራት ትልቅ ነው የምንለው በቅድስት ቤተክርስቲያን አውደ ምህረት በመቆም ቃለ እግዚአብሔርን የሚያስተላልፍ በመሆኑ ነው። ዘጸዐ 19፤1022

በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም <u>ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ህይወቱን</u> መቀደስ አለበት።

- ውስጣዊ ህይወት ውጫዊ ህይወት ስንል ምን ማለት ነው?
- ህይወትህ/ሽ ምን ይመስላል ለመረሃ ግብር መሪነት በቂ/ተስማሚ ነው?
- አንተ ስትቆም ለሰው ህይወትህ ምን ያስተምራል?
- አውደምህረት ስትቆምና መረሃ ግብር ጨርሰህ ስትወጣ/ሚ ስትገባ/ መንፈሳዊ ግብር/ህይወትህ; ልክ አውደምህረቱ እንደነበርከው ነው?
- እግዚአብሔር አንተማህ ቢልህ ምን ትላለህ?

ካህናት ህዝቡን አስከትለው ቀድመው ለቤተ መቅደስ ቅርብ ስለሆኑ መጀመሪያ ራሳቸውን መቀደስ አለባቸው። ምክንያቱም የሚቀርቡት ቦታ ታቦተ ህጉ የሚገኝበት የአምላካችን ክቡር ስጋውና ቅዱስ ደሙ የሚፈተትበት ጸሎታችን የሚያርግበት በረከትን የምንቀበልበትና ክብርን የምንጎናጸፍበት ልዩ ስፍራ ስለሆነ ነውና። ?

ስለዚህ በዚህ ቅዱስ ስፍራ ሆኖ/ቆሞ/ የሚያገለግል ሰው/ለማገልገል የሚፈልግ ሰው/ ንጽህና ቅድስና ገንዘቡ ማድረግ ግዴታው ነው። በክፋት በርኩሰትና በክህደት ላይ ሆኖ ለሰውም መሰናክል እየሆኑ አገለግላለሁ ማለት በደል መጨመር ነው ማቴ 18፤6 በእኔ ከሚያምኑት ከታናናሾች አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ <u>የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ</u> (ትረጓሜ ይመልከቱ) ታስሮ ወደ <u>ጥልቅ ባህር</u>(ትረጓሜ ይመልከቱ) መስጠም ይሻለው ነበር-----ማሰናከያ ለሚያመጣ ለዚያ ሰው ወዮለት። ስለሆነም በህጢአት ውስጥ ያለ ሰው ንስሃ ገብቶና እየገባ ከክፋ ስራው ተመልሶ ይህንን አገልግሎት ማገልገል ይጠበቃል። ስለዚህ በመረሃ ግብር አገልግሎት የሚያገለግል ሰው ንስሐ እየገባ ቅዱስ ስጋውንና ክቡር ደሙን እየጠጣ ቢያገልግል ለጉባኤውም መሳካት ፍሬም ለማፍራት የተሳካ ይሆንለታል።

መረሃ ግብር መሪ፡-

1. የሚታዘዝ ይሁን፤- መታዘዝ ክርስቲያን በህይወት ዘመኑ ሲፈጽመው የሚኖር መልካም ምግባር ነው።እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥረው አዘዥና ታዛዥ አድርጎ ነው ይህም ታዛዥነቱ ለእግዚአብሔር አዘዥነቱ ፍጡራንን ነው።አዛዥነቱ ዘፍ 1፡26-28 እግዚአብሔርም አለ---የባህር አሳዎችንና የሰማይ ወፎችን እንስሳትንና <u>ምድርን ሁሉ</u> በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ---በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዟቸው። ታዛዥነቱ ዘፍ 2፡16-17 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ <u>አዘዘው</u> ---። ስለዚህ ሰው፡-
   - ለፈጠረው ለአምላኩ ይታዘዛል
   - እርሱን መስሎ ለተፈጠረ ሰው ይታዘዛልም ያገዛልም
   - ለመላዕክት ይታዘዛልም ያገዛልም
   - በሌሎች ፍትረታት ላይ ግን አዛዥ ይሆናል (ይህ ሊሆን የሚችለው ግን መጀመሪያ ሰው ለአምላኩ ፍፁም ታዛዥ ሲሆን ብቻ ነው)። መታዘዝ ከመንፈሳዊ ፍሬዎች ውስጥ አንዱ ነው ለቅድስና የሚያበደርስ የአገልግሎት እሴት ነው። ዘፍ 22፡17 አብርሃም ስለታዘዘ በረከት አግኝቷል።

     መታዘዝ፡-
     - በረከትን እንድወርስ ያደርገናል ዘፍ ዘፍ 22፡17 የአብርሃም መታዘዝ
     - ለሐዋርያነት ያበቃል፡ ነብያት፤ሐዋርያት ሊቃውንቱ---
     - ሀሴትን ይጨምራል

- ፅድቅንያስገኛል ሮሜ 4፡ 1- ፍጻሜ አብርሃም በእምነት መታዘዙና ውጤቱ-----
- ለመከራ ይዳርጋል ት/ዮናስ 1፡1-ፍፃሜ

  አለመታዘዝ፡-
- ከተቀደሰችው ምድር ያስባርራል ያስረግማል ዘፍ 3፡1-ፍፃሜ
- ድካምን ያመጣል፡ አዳም ባለመታዘዙ በወዙ እንዲበላ ሆኗል።
- ጨካኝነትን እንድንማር ያደርገናል ዘፍ 4፡1-ፍፃሜ የቃየል አለመታዘዝና ፍፃሜው
-

2. ትህትናን መላበስ አለበት፡- ትህትና ራስን ዝቅ ዝቅ ማድረግ ወይም ማዋረድ ማለት ነው።ትህትና የበታችነት ስሜት ሣይሆን ኩራትን፤ትእቢትን፤ኩራትንና በከንቱ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግን ማስወገጃ መንገድ ነው። ትህትና የመታዘዝ የመንፈስ ፍሬ ነው። እግዚአብሔር በቅዱሳን ይታዘዛል(ምን ማለት እንደ ሆነ ተነጋገሩበት)። እግዚአብሔር እስከሞት የታዘዘ ሆነ የብህርይ አባቱ አብ አዝዞት ወደ ምድር መጣ (በሥላሴ ዘንድ ማዘዝና መታዘዝ አለ ወይ ተወያዩበት)። እግዚአብሔር ታዝዟል። እግዚአብሔር ሰውን ነማዳን የመጣበት የትህትና ፍሬ ነው። ቅዱሳን እያወቁ አናውቅም እየቻሉ አንችልም ጥበብ እያላቸው የለንም ኃጢአተኛ ሳይሆኑ ኃጢአተኛ ነን የሚሉት ገና ሩጫቸውን ስላልጨረሱ፤ አንድም ጥበብ እውቀት ቅድስና ስጦታ እንጅ የእነሱ ስላልሆነ፤ አንድም የራስ ሃይማኖት(እምነት) ይመሰከራል እንጅ የራስ ስራ በራስ ስለማይመሰከር ምስክርነትን የሚሰጥ አምላክ ስለሆነ ነው። በትህትና ህይወት የኖሩና በእርሷ የተመላለሱ ቅዱሳን ብዙዎች ናቸው፤ ለምሳሌ፡-
   - ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያንን ከማሳደድ ተመልሶ በሀዋርያዊ አገልግሎት መሰማራቱ አስራአራት(14) መጻሕፍትን መጻፉ እስከሦስተኛው ሰማይ መነጠቁ በጨርቁ ሳይቀር ድውያንን መፈወሱ ---ይህ ሁሉ መልካም ስራው ሣያስመካው ራሱን ዝቅ በማድረግ ከሁሉም በኋላ ጭንጋፍ ለምመስል ለእኔ ታየኝ። 1 ቆሮ 15፡8
   - አበ ብዙሃን አብርሃም ከሀገሩ ከወገኑ ተለይቶ እግዚአብሔር ወደ አመለከተው ምድር በመሄድ እንግዶችን በመቀበል መትጋቱ ሥላሴን እንግድነት መቀበሉ ልጅህን ሰዋልኝ፤ ሲባል ለመስዋት ማቅረቡ---ሁሉ አላስመካውም ከእግዚአብሔር ጋር በአደረገው ንግግር---እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ከእግዚአብሔር ጋር እናገር ዘንድ አሁን ጀመርሁ ዘፍ 18፡26
   - እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የባርያውን ትህትና ተመልክቷል ሉቃ 1፡48

ቅዱሳን በቅድስና ህይወት እየተመላለሱ ስራቸው ሳያስመካቸው በትህትና ውስጥ እየኖሩ መረሃ ግብር መሪውም ከቅዱሳን ህይወት ትምህርት በመወሰድ ትህትናን ተላብሶ ከትዕቢት ርቆ ማገልግል ይኖርበታል። በምዕመናን ፊት ቆሞ መረሃ ግብር ስለመራ ራሱ ጻድቅ ወይም ትልቅ አድርጎ መቅጠር የለበትም። ሉቃ 14፡7 ራሱን ከፍ የሚያደርጉ ሁሉ ይዋረዳል ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ከፍ ይላል። ጌታችንም እኛን ዝቅ ማለትን ሊያስተምርን በከብቶች ግርግም ተወለደልን፡የሐዋርያትን እግር አጠበ፡ሁሉን እየቻለ መከራን ተቀበለልን። ሊቃውንቱም እንዲህ ያለ ትህትና እንደምን ያለ ነው እያሉ አወድሰውታል (ቅዳሴ ዮሃንስ አፈወርቅ ቁ.45)። ደግሞም ትህትናን ከእኔ ተማሩ በማለት አስተምሮናል ማቴ 11፡29 ኢሳ 53፡7-9 1 ጴጥ 2፤21-25

3. ከትዕቢት መራቅ አለበት፡- ትዕቢት ማለት ትምህክት ኩራት ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ማለት ነው።በመጽሐፍ ቅዱስ ስለትዕቢት ተጽፎ እናገኛለን። ምሳ 16፡5 በልቡ የታበዬ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ እርኩስ ነው። ያዕ 4፡6 እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሁታን ግን ጸጋውን ይሰጣል። ከዚህ ተጨማሪ 2 ጢሞ 3፡4 1 ጢሞ 3፡6 ሮሜ 12፡3 ማር 7፡22 መዝ 30፡23፤ 110፡5-7 ምሳ 11፡2-------

   ትዕቢት የሚሰራባቸው መንገዶች፡-
   - ሀብት ዘፍ 28፡22
   - መልካም ስራ ሉቃ 17፡10
   - ጉልበት
   - ዘር
   - እውቀት
4. የሚነበብ መጽሐፍ መምሰል አለበት፡- መንፈሳውያን መጽሐፍት ሲገለጡ ሃይማኖትንና በጎ ምግባርን እንድከተልና እንድንሰራ እንደሚመክሩን መረሃ ግብር መሪም ውጫዊ ህወቱ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ ህይወቱ ሲገለጥ ቅንነት የዋህነት አስተዋይነት፤ትሁት ትሕስተኛ፤እልከኛ ያልሆነ፤ሰውንም እግዚአብሔርንም የሚወድ፤ሃይማኖቱ የጸና ምግባሩ የቀና መሆን ይገባዋል። ሰውን ማስተማር የሚቻለው በቃል ብቻ ሳይሆን በበጎ ምግባር ቄምርም ነው እንጂ። ለዚህም ነው ምግባር ታላቅ ሐዋርያ ናት የሚባለው።. ማቴ 5፤13-16 ሉቃ 12፡35 መልካም ስራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ።
5. ከክፉ ሰዎች ጋር ባለእንጀራነትን መመስረት የለበትም፡- 1 ቆሮ 15፡33 ክፉ ባለንጀርነት መልካሙን አመል/ፀባይ/ ያበላሻል። ብሎ እንደተናገረው በምግባራቸውና በሃይማኖታቸው መጥፎ ከሆኑ ሰዎች ጋር የምንመሰርተው አግባብ ያልሆነ አቀራረብ መልካም ፀባያችንን አስትቶ የመጥፎ ግብራቸው ተባባሪ ያደርገናል። በዚህ ኃጢአት ተሰንካክለው የወደቁ ብዙዎች ናቸው።

   ለምሳሌ፡-
   - ሮብዓም መጥፎ በሆኑ እስራኤላውያን 1 ነገ 12፡1
   - አምኖን በመጥፎ ጓደኛው ዮናዳብ 2 ሳሙ 13፡1

- ሔዋን ምክረ ከዩሴን ሰምታ ዘፍ 3፥1-8
- ሐናንያና ሰጲራ ሥራ 5፥1-11

በአጠቃላይ የሰይጣን መንፈስ ያለባቸው ሰዎች ምግባራቸው የከፋ ሃይማኖታቸው ክህደት ኑፋቄ የበዛበትእንዲሆን የሚገፋፋና የሚያስተምሩ አሎ። ኤር 5፥26

በዚህ ክፉ ምክር እንዳንወድቅ፦ ምሳሌ

- እቪአትበል፥1፥10-19 ልጄ ሆይ ዝንጉዎች ሰዎች አያስቱህ እሽም አትበላቸው ና ከእኛ ጋር ደም በማፍሰስ አንድ ሁን ጻድቅ ሰውም በመድር እንቅበር ብለው ቢማልዱህ -----ከእነርሱ ጋር በመንገድ አትሂድ።-----ይህ መንገድ ኃጢአትን የሚፈጽሙ ሁሉ ነው።
- እንደ ዮሴፍና እንደ ሶስና እምቢ በል፦ ዘፍ 39፥7-18 ዳን 13፥1-ፍፃሜ ስለዚህ መረሃ ግብር መሪውም የሚሰተላልፈውና በህይወቱ ክቡር የእግዚአብሔር ቃል የያዘ በመሆኑይህንን የከበረ ነገር ተሸክሞ ክፉ ስራ ሊሰራ አይገባውም። አንድ መረሃ ግብር መሪ ከክፉ ሰዎች ጋር ባለእንጀርነትን ቢመሰርት መጀመሪያ የሚጎዳው ራሱን ነው ቀጥሎም በማህበሩ ላይየሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም።
  ለምሳሌ አካን የተባለው ሰው እርም የሆነውን ነገር በመስራቱ እግዚአብሔር ተቆጥቶ እስራኤላውያንን በጠላቶቻቸው አንዲሸነፉ አህዛብ ሊያጠፉን ነው ብለው እንዲጨነቁና እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም እስኪላቸው ደርሰው ነበር ኢሳ 7፥1 ስለዚህ መረሃ ግብር መሪውም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እርም(የጠከለከለ) የሆነውን ነገር ከክፉ ባለእንጀሮቹ ጋር ተባባሪ ሆኖ(ተሰነካክሎ ወድቆ) ሰርቶ እንዳይወድቅና ለማጎበሩም እንዳይተርፍ ሁልጊዜ ሊጠነቀቅ ይገባዋል። ምክንያቱም ወፍጮ ቤት ገብቶ ዱቄት የማይነካው በጥዋት ተነስቶ ብርድ የማይነካው፤ በጋው መጥቶ ሙቀት የማይጨምርበት ሰው የለምና ክፉ ባለእንጀራም መልካሙ አመል ሳይቀይር ዐይሄድምና መጠንቀቅ ይገባል

6. በጸሎት ህይወት መትጋት አለበት፥-ጸሎት በሁለት ይከፈላል 1. የግል ጸሎት 2. የማህበር ጸሎት አንዳደም የቤተሰብ ጸሎት ሲጨመርበት ሶስት ይሆናል። ጸሎት ከቅጽረ-ቤተክርስቲያንና ከቅጽረ-ቤተክርስቲያን ውጭ የጸለያል።

   ጸሎት

   - በቃል የተያዘውን፤
   - በመጽሐፍ የሰፈረውን፤
   - የራስን ልመናና ምስጋና ይደረጋል።
   - በንባብ በዜማና በለሆሳስ ለፈጣሪ በማቅረብ ከልዑል እግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት መንፈሳዊ ድልድይ ነው።

     ጸሎት የአፈጻጸሙ መንገድ ቢለያይም አላማው ግን

     - የምንፈልገውን የምንቀበልበት
     - ያጣነውን የምናገኝበት
     - የራቀውን የምናቀርብበት
     - የመረረውን የምናጣፍጥበት
     - አጋንንትን ድል የምንነሳበት
     - ኃይል መንፈሳዊ የምናገኝበት
     - አምላካችንን የምናመሰግንበት ----- ነው።

     ጸሎት ጥቅሙ

     - ኃይል ታሰጣለች ያዕ 5፥16
     - አጋንንትን ታስወጣለች ኤፌ 6፥10
     - ሙት ታስነሳለች 1 ነገ 17፥17
     - ድውይ ትፈውሳለች ስራ 3፥1
     - ዓይን ታበራለች ስራ 3፥1
     - ባህር ትከፍላለች ታሻግራለች 2 ነገ 2፥8-14 ዘጸ 14፥15 ኢያሱ 3፥14
     - እድሜ ታስጨምራለች 2 ነገ 20፥1
     - ዝናብ ታዘንማለች ታቆማለች 1 ነገ 17፥1 18፥1

በአጠቃላይ ጸሎት አምላካዊ ስጦታ ናት። ስለዚህ መረሃ ግብር መሪው እንደ አለት በመንፈሳዊ ህይወቱ ይጠነክር ዘንድ በጸሎት ህይወት መትጋት አለበት።

አንድ መረሃ ግብር መሪ/መምህር/ በጸሎት ህይወት የሚተጋ/የሚበረታ/ ከሆነ፥-

- ለአገልግሎት ሲተጋ ውጤታማ ይሆናል
- የአባቶቹን ስራ ይሰራል
- በሃይማኖት ይጸናል በምግባር ይበረታል

- ❖ ከሓጢአት ይርቃል
- ❖ በቅድስና ህይወት ይመላለሳል
- ❖ መንፈሳዊ ተምኔቱ እንደ አባ ዲመጥሮስ፤ አባ ህርያቆስ፤ ቅዱስ ኤፍሬም፤ አባ ጊውጊስ ዘጋስጫ ይፈጸምለታል።
- ❖ ከፈተናም ይጠበቃል ማቴ 26፡41

7. ቃለ እግዚአብሔርን እለት እለት መማር አለበት፡- ቆላ 3፡6 በጥበብ ሁሉ እንድትበለጽጉ የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ዘንድ ይጽና በመንፈስ ራሳችሁን አስተምሩ። በማለት እንደተናገረው መረሃ ግብር መሪ የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ጠንቅቆ መረዳት አለበት።

   ምን ምን መማር/ማወቅ/ አለበት ከተባለ፡-
   - ✓ ትምህርተ ሃይማኖትን
   - ✓ ስርዓተ ቤተክርስቲያንን
   - ✓ ስለነገረ ቅዱሳን/መላዕክት
   - ✓ ትውፊትን
   - ✓ የሚኖርበትን አካባቢ/ማህበረሰብ/ ማወቅ/መረዳት አለበት።

አንድ መረሃ ግብር መሪ መረሃ ግብር ለመምራት ከእርሱ በፊት ከነበሩት ወይም አብረውት ካሉት የቤተክርስቲያናችን አስተምህሮዎች መማርና ማወቅ አለበት። ስለዚህ አንድ መረሃ ግብር መሪ የእግዚአብሔር ጉባኤ ለመምራት ቅድሚያ ሊኖረው የሚገባው ነገር የሚከተሉት ናቸው

- ✍ እውቀት
- ✍ ፈሪሃ እግዚአብሔር
- ✍ ቅድመ ዝግጅት ያስፈልጉታል።

  እነዚህ የሌሉት ሰው መረሃ ግብር ቢመራ፡-
  - ምስጢር ያዛባል
  - ስርዓት ያፋልሳል
  - ሰው ያሰናክላል
  - ራሱም ለቅጣት ለሚያደርስ ሃጢአት ይደርሳል።

አባቶቻችን መምህሮቻቸውን እስከመተካት የደረሱትና ለታላቅ ክብር የደረሱት ከመምህር ተምረው ነው።

- ✍ ኢያሱ ከሙሴ
- ✍ ኤልሳ ከኤልያስ
- ✍ ሀዋርያት ከጌታችን
- ✍ ጢሞቲዎስ ከጳውሎስ ----------ሌሎችም ሁሉ ተምረው ለክብር ለመሪነት ለመምህርነት በቅተዋል።

ቃለእግዚአብሔርን የምንማራባቸው መንገዶ

- ✍ ከመምህራን ቃል በቃል በመረዳት(በማስተረጎም)
- ✍ ሊቃውንት ቤተክርስቲያን ከትበው ካስቀመጡት መጽሐፋቸው በማንበብ (የተተረጎመውን ማንበብ)
- ✍ ተፍጥሮን በማየት/በመመራመር/ እንደ አብርሃም እንደ ሙሴ ጸሊም/

8. ተጠራጣሪ መሆን የለበትም፡- ጥርጥር አለማመን አለመታመን መንታ መንገድ ላይ ቆሞ ነው ወይስ አይደለም እያሉ ማመንታት ማለት ነው። የጥርጥር መንፈስ የሚመጣው የእምነት ጽናት ጉድለት ሲኖር ነው። ጥርጥር ያለበት ሰው በህይወቱ፡-
   - ጭቅጭቅ
   - ሰላምን ማጣት
   - እንቀልፍ መከልከል
   - ግራ መጋባት፤የተከፈለ ሃሳብ
   - ልጸረጋጋ ህይወት እንዲኖረው ያደርገዋል።
9. ከንቱ ውዳሴ የሚጠላ መሆን አለበት፡- ውዳሴ ከንቱ ማለት ከሰው ዘንድ ዝናን እይታን ሙገሳን አድናቆትን ሽቶ/ፈልጎ መንፈሳዊ አገልግሎት ማከናወን ማለት ነው። ፊል 2፡3 ሉቃ 17፡10 አንድ መረሃ ግብር መሪ ማገልገል ያለበት ይህንን ፈልጎ ሳይሆን እግዚአብሔር የሚሰጠውን ሰማያዊ ዋጋ እያሰበ መስራት ይኖርበታል።
10. የመንፈስ ፍሬዎችን የተላበሰ መሆን አለበት፡- ገላ 5፤22 ያሉትን መተግበር አለበት

11. ተሃድሶ መናፍቃንን የሚገታ/የሚከላከል መሆን አለበት፡- ተሃድሶ የሚባሉት የቤተክርስቲያን ስርዓት ዶግማ እንደዚህ አልነበርም ተቀይሯል እንመልሰው እናስተካክለው ወይም ደግሞ የቤተክርስቲያን ህግና ስርዓት አርጅቷል(አሮጊቷ ሳራ) በአዲስ ስርዓት እናዘጋጀው እያሉ በቤተክርስቲያን ውስጥና ውጭ ሆነው ቤተክርስቲያንን የሚያውኩና የሚበጠብጡ መናፍቃን ናቸው። ስለዚህ መረሃ ግብር መሪ የመናፍቃንን ግብራቸውን አውቆ ሊቃወማቸው ይገባል። እንዲህ ሲባል ግን ይህ ድርሻ የመረሃ ግብር መሪው ብቻ ነው ለማለት አይደለም ለሁሉም ነው እንጂ።
12. በአንደበቱ ክፉ ከመናገር የሚጠላ መሆን አለበት፡-
13. በዝሉት እንዳይወድቅ መጠንቀቅ አለበት፡-
14. ጤናማ ካልሆነ የፆታ መቀራረብ መራቅ አለበት፡-

13-14 ያሉትን ተወያዩባቸው
- ✓ በአንደበት ሀጢዓት እንዴት ይሰራል?
- ✓ ዝሉት ማለት ምን ማለት ነው?
- ✓ ፆታዊ መቀራረብ እንዴት ሐጢአት ይሆንል ሁሉንም ምሳሌ በመስጠት አብራሩ?

ምዕራፍ አራት
ስለመረሃ ግብር አመራር

ቤተክርስቲያን ተልዕኮዋን ለመፈፀም

- ስርዓት ሰርታ
- ህግ አውጥታ
- በትምህርተ ወንጌልና በስርዓተ ጸሎቷ ሁልጊዜ በአግባብ በስራዓት ታከናውናለች።

በቤተክርስቲያን የተዘጋጀ መረሃ ግብር መሪዎች በሁለት ይከፈላሉ

1. በጋራ የተመደቡ
2. በተናጠል የተመደቡ ናቸው።

በኪዳን በጸሎተ ኪዳን፤በሰዓታት፤በማህሌት፤የውዳሴና የቅዳሴ ማረያም ጸሎት፤ በሚደረግበት ጊዜ የሚመሩ መረሃ ግብር መሪዎች በቤተክርስቲያን አጠራር ፡- ቄሰ ገበዝ፡ሊቀ ዲያቆን፡አጋፋሪ ቀኝ ጌታ፡ጋራ ጌታ፡ ሊቀ ጠበብት፤ መሪጌታ...እየተባሉ የጠራሉ።

አንድ መረሃ ግብር መሪ መረሃ ግብር ለመምራት ሊያሟላቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነገሮች

- ❖ በቂ እውቀት ሊኖረው ይገባል
- ❖ መንፈሳዊ ህይወቱ የተስተካከለ ሊሆን ይገባል
- ❖ ነውር ነቀፋ የሌለበት ሊሆን ይገባል
- ❖ ለመምራት ስልጠና መውሰድ አለበት
- ❖ በሶስቱ ጊዚያት የሚከናወኑ ተግባራትን ማወቅ አለበት
  - ቅድመ አውደ ምህረት
  - ጊዜ አውደ ምህረት
  - ድህረ አውደ ምህረት
    - ቅድመ አውደ ምህረት
      - ✍ በጸሎት ህይወት መኖር
      - ✍ ስለመረሃ ግብሩ ዝርዝር መረዳት፡- ይህም የመረሃ ግብሩ አላማ፤ የመረሃ ግብሩ ዝርዝር የአለቱ መረሃ ግብር፤ የታዳሚዎችን ሁኔታ ማወቅ አለበት።
      - ✍ ቀኑን ሰዓቱንና ቦታውን ማወቅ
      - ✍ ጉባኤው ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ መገኘት
      - ✍ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን አስቀድሞ ማሟላት

- ✍ የስነ ልቦና ዝግጅት ማድረግ
- ✍ የሚለበሰውን አልባሳት ማዘጋጀት
- ✍ ስለራሱ ወይም ስለሌሎች ላለመናገር መዘጋጀት

ምዕራፍ አምስት

ጊዜ አውደ ምህረት

ጊዜ አውደ ምህረት የምንለው መረሃ ግብሩ በጸሎት ተጀምሮ በጸሎት እስኪፈጸም ድረስ ያለው ጊዜ በመሆኑ መረሃ ግብር መሪው ቅድማ ዝግጅት ሲያደርግ የነበረውን በተግባር የሚያውልበት ጊዜ ነው።

ስለዚህ ይህ መረሃ ግብር መሪ፡-

- ❖ ስርአተ ቤተክርስቲያን የጠበቀ ልብስ ለብሶ መምራት
- ❖ በስመ ስላሴ ማማተብ
- ❖ በእግዚአብሔር ስም ሰላምታ ማቅረብ
- ❖ በጸሎጽ መጀመር
- ❖ የእለቱን መረሃ ግብሮች በዝርዝር ማሳወቅ
- ❖ በመዝሙርና በአሳታፊ ነገሮች ጊዜውን ሚዛናዊ ማድረግ
- ❖ ሰአትን መጠበቅ የሚገባው
- ❖ ከአውደ ምህረት አካባቢ መራቅ የማይገባ መሆኑን ማወቅ ያለበት
- ❖ ከስብከት ወይም ከመዘሙር በኋላ የሚናገረውን ንግግር መለየት
- ❖ የሚናገርበት ቋንቋ ኦርቶዶክሳዊ መሆን
- ❖ በትዕግስትና በእርጋታ የሚቆም
- ❖ የሰውነት እንቅስቃሴዎቹ የተመጠኑ መሆን
- ❖ የተመጠነ ንግግር ማድረግ
- ❖ አርአያ ክህነትን የሚያሳይ
- ❖ መረሃ ግብሩን ለመምህሩና ለመንፈስቅዱስ እለቃለሁ የማይል
- ❖ የማሳረጊያ ጸሎት ማስደረግ

ምዕራፍ ስድስት

ድህረ አውደ ምህረት

ድህረ አውደ ምህረት የምንለው መረሃ ግብሩ መርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ያለውን ነው።

መረሃ ግብር መሪ በዚህ ጊዜ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች፡-

- ❖ እግዚአብሔርን ማመስገን
- ❖ ስህተቱን ማረም/ማስተካከል
- ❖ በከንቱ ውዳሴ እንዳይወድቅ መጠንቀቅ
- ❖ መልዕክት ማስተላለፍ
- ❖ በጸሎት ማሰናበት
- ❖ ማሰናበት

ከአውደ ምህረት ውጭም በልዩ ልዩ መንገድ ራሱን ማንቃትና መጠበቅአለበት ።

-

ምዕራፍ ሰባት

ለመንፈሳዊ ጉባኤዎችና ለመረሃ ግብር መሪዎች ሚና

የሰንበት ትምህርት ቤቶች አስተዋጽኦ

ምዕራፍ ስምንት

ተግባር

ይህ ትምህርት ከተጠናቀቀ ሁሉም አባላት ልምምድ ያደርጋሉ።